# በፌዴራል ጤና ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
# ዜና ኢሕጤኢ

ህዳር 2014 ቅጽ 5 ቁጥር 8

በኢ.ሕ.ጤ.ኢ. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ


## በእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት ተከናወነ



የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና እንስቲትዩት ከጤና ሚኒስቴር እና ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር በእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት አከናወነ፡፡ የተከበሩ ዶ/ር መሰረት ዘላለም በጤና ሚኒስቴር የእናቶችና ህጻናት ጤና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ላይ የሚሰሩ ስራዎች ይበልጥ ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው አሳስበው የአንድ ሀገር እድገትና ብልጽግና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከእናቶችና ጨቅላ ህጻናት ጤና ጋር እንደሚያያዝ አስረድተዋል፡፡

ዶ/ር ቴዎድሮስ ጌታቸው በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና እንስትቲዩት የሥርዓተ ጤና እና ሥነ-ተዋልዶ ምርምር ዳይሬክተር በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር አውደ ጥናቱ ላለፉት ሠላሳ ዓመታት በጤናው ሴክተር በተለይ በእናቶችና ህጻናት ጤና ዙርያ የተመዘገቡ ውጤቶችን ለማሳየትና የነበሩ ክፍተቶችን ለመለየት እንዲሁም በቀጣይ በተለይ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችን ለማሳካት መከናወን ባለባቸው ዋና ዋና ክንውኖች ዙርያ እንደሚያተኩር ገልጸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና እንስትቲዩትና የጤና ሚኒስቴር ካውንት ዳውን 2030 ከተባለ በእናቶችና ህጻናት ጤና ላይ ከሚሰራ የጥናት ቡድን ጋር በመተባበር በቀጣይ የጥናት ውጤቶችን በመገምገም ግንኙቶችን የማዳበር ስራዎች እንደሚከናወኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአውደ ጥናቱ ላይ ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይቶች ተካሂደባቸዋል፡፡

## “በስነምግባር የታነፀ አመራር ከሙስና ለፀዳች ኢትዮጵያ!” በሚል 18ኛው የጸረ ሙስና መከላከል ዓመት ተከበረ



የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት በዓለም አቀፍ ደረጃ 18ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ 17ኛ ጊዜ የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስናን ቀን “በስነምግባር የታነፀ አመራር ከሙስና ለፀዳች ኢትዮጵያ!” በሚል መሪ ቃል በኢንስቲትዩቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ አከበረ፡፡

በመድረኩም የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አማካሪ ዶ/ር አማር በርባ መግቢያ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸውም ሙስና ልማትን በማዳከም የሀገርን ዕድገት የሚያቀጭጭና ድህነትን የሚያባብስ የብልጽግና ካንሰር በመሆኑ ይህ ችግር ከሌሎች አህጉራት በይበልጥ አፍሪካ በስፋት ስለሚስተዋል ይህንንም የልማት፣ የሰላምና የብልጽግና ጠንቅ ማስወገድ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት በመሆኑ በየደረጃው ያለው አመራር ሀገራችን በውስጥም ከውጪም

. . .ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# የዓለም ዓቀፍ የጤና ደንብ አተገባበር የአቅም ግንባታ ሪፖርት አውደ ጥናት ተካሂደ



የኢንስቲትዩቱ የዓለም ዓቀፍ የጤና ደንብ አተገባበር የአቅም ግንባታ ሪፖርት ለማዘጋጀት የተለያዩ ተጠሪ መስሪያ ቤት ተወካዮች በተኙበት ከህዳር 15 እስከ 17/2014 ዓ.ም በአዳማ ከተማ አውደ ጥናት አካሄደ።
አቶ አስቻለው አባይነህ የኢንስቲትዩቱ ም/ዋና ዳይሬክተር በአውደ ጥናቱ ላይ ተገኝተው እንደ ገለጹት እንደ ሃገር የተገባውን ቃል ኪዳን ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው።ተልዕኳችንም ህይወትን ማዳን ነው፤ነገር ግን ካለፈው ዓመት ጀምሮ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሁሉም ዘርፍ ሙሉ በሙሉ ልናሳካቸው ያቀድናቸውን ስራዎች እንዳንሰራ ከማድረጉም በላይ አሁን ሃገራችን ያለችበት የውስጥና የውጪ ጫናዎች በጤናው ዘርፍ መድረስ የሚገባን ላይ እንዳንደርስ እንቅፋት ሊፍጥር ቢችልም ባደረግነው ቅንጃታዊ ስራ ወደኋላ አልተመለስንም ሲሉ ተናግረዋል።
ም/ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘው በሁሉም ተቋማት የተሰሩ ስራዎችን በመገምገምና በመፈተሽ ክፍተት የታየባቸውን ጉዳዮች ምን ብናደርግ በተሻለ መንገድ ልንፈታቸው እንችላለን የሚሉትን በመወያየት እና የጋራ እቅድ በማውጣት ወደስራ መግባት ያስፈልጋል።እንዲሁም በሃገራችን ላይ የተደቀነውን የውጭና የሃገር ውስጥ ጫና ውጤታማ ስራ በማስመዝገብ ማሸነፍ እንደሚገባ በአጽንኦት አስገንዝበዋል።
ዶ/ር ፈይሳ ረጋሳ የአለም አቀፍ የጤና ደንብ የኢትዮጵያ ተጠሪ በበኩላቸው 196 ፈራሚ አገሮች ለአለም አቀፍ ጤና ድርጅት ጉባኤ የደንቡን አተገባበር የአቅም ግንባታ ሪፖርት ማቅረብ ግዴታ መሆኑን ጠቅሰው በዚህ ምክንያት የሃገራችንን ሪፖርት ለመላክ ከ15 በላይ የሚሆኑ ተጠሪ መስሪያ ቤቶች በአውደ ጥናቱ ላይ መሳተፋቸውንና ሪፖርቱ በባለሙያ ደረጃ መዘጋጀቱንና በቀጣይ በከፍተኛ አመራሩ ታይቶ ከጸደቀ በኋላ የሚላክ መሆኑን ገልጸዋል።
በአለም አቀፍ መስፈርት መሰረት በአለም አቀፍ እና በአፍሪካ ደረጃ የ2014 ዓ.ም ሪፖርት ሳይጨምር የተካታታይ የ3 ዓመታት ሪፖርት ከአማካይ ውጤት በላይ መሆኑን ገልጸው ውጤቱም በሃገር ደረጃ የተሻለ ስራ መሰራት እንደሚያስፈልግ አመላካች መሆኑን ዶ/ር ፈይሳ ረጋሳ ጨምረው አብራርተዋል።
በአውደ ጥናቱ ላይ የተለያዩ ጥናቶች ቀርበው ሰፊ ግምገማና ውይይት ከመደረጉም በላይ በአለም አቀፍ የጤና ደንብ የአቅም ግንባታ መስፈርት መሰረት የሃገሪቱ የጤና ደረጃ በምን ላይ እንደሚገኝ በቀረቡት የአለም አቀፍ የጤና ደንብ መጠይቆች በአወደ ጥናቱ ተሳታፊ በነበሩ የተጠሪ መስሪያ ቤት ባለሙያዎች የተሞሉ ሲሆን የግምገማ ሪፖርቱ በከፍተኛ አመራሩ ታይቶ ከጸደቀ ባኋላ ለአለም ጤና ድርጅት ጉባኤ የሚላክ ይሆናል።

# ለጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን የደም ልገሳ ተከናወነ



የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ሠራተኞች እና የማኔጅመንት አባላት ህዳር 15 ቀን 2014 ዓ.ም ለጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን የደም ልገሳ አከናወኑ
በደም ልገሳው ሥነ-ሥርዓት ላይ ደም የለገሱት ሠራተኞች እንደገለፁት ለጀግናው መከላከያ ሰራዊት ደም ከመለገስ በተጨማሪ በሁሉም ዘርፍ ደጀን ለመሆን የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በማንኛውም ጊዜ ለማከናወን ፍቃደኛ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።
የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ቀደም ብሎ የገንዘብ እና የልዩ ልዩ ቁሳቁሶች እርዳታ ያደረጉ ሲሆን በቀጣይም ይኸው የደጀንነት ተግባር የሀገራችን ሰላምና ህልውና በአስተማማኝ ሆኔታ እስከሚረጋገጥ ድረስ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

# አገር አቀፍ የስርዓተ ምግብ ምርምር አውደ ጥናት ተከካሄደ






የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የምግብ እና ስነ-ምግብ ምርምር ዳይሬክቶሬት እና የብሔራዊ የስርዓተ ምግብ የመረጃ ማዕከል በጋራ በመሆን ከህዳር 29 እስከ ታህሳስ 1/2014 ዓ.ም የሚቆይ ሀገር አቀፍ የምግብ እና የስርዓተ ምግብ ምርምር አውደ ጥናት በአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል አካሄዱ።
የአውደ ጥናቱ ዋና አላማ በምግብና ስነ-ምግብ ዙሪያ የተሰሩ የተለያዩ የምርምር ውጤቶች በአውደ ጥናቱ ላይ ቀርበው ለፖሊሲ እና ለፕሮግራም አውጪ አካላት መረጃ ላይ መሰረት ያደረጉ ግብዓቶችን ማቅረብ ነው።
ዶ/ር ሊያ ታደሰ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር በአውደ ጥናቱ መክፈቻ ስነ -ስርዓት ወቅት እንደተናገሩት በአውደ ጥናቱ ላይ የምግብና የስርዓተ ምግብ እስትራቴጂ አፈጻጸምን በከፍተኛ ደረጃ ሊያግዙ የሚችሉ እንዲሁም የተለያዩ ፕሮግራሞችን ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶች የሚቀርቡ መሆኑን፣ በተለይም በምግብና ስርዓተ ምግብ ዙሪያ ያሉትን በርካታ ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችሉ የጥናትና ምርምር ውጤቶች እንደሚቀርቡ ገልጸዋል፡
ዶ/ር ጽጌረዳ ክፍሌ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር በበኩላቸው ኢንስቲትዩቱ በሃገር አቀፍ ደረጃ በርካታ የህብረተሰብ የጤና አገልግሎት ስራዎችን እንዲሰራ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን ጠቅሰው በምግብ እና ስነ- ምግብ ዙሪያ ያሉ የተለያዩ ችግሮችን ለመፍታት በርካታ የምርምር ስራዎችን ተቋሙ እየሰራ መሆኑን አብራርተዋል።
አውደ ጥናቱ ለተመራማሪዎች፣ለፖሊሲ እና ፕሮግራም አውጪዎች በመረጃ ግበዓትነት የሚያገለግሉ በርካታ የጥናት ውጤቶች እንደሚገኙ፣እንዲሁም ለምግብና ስርዓተ ምግብ እስትራቴጂ አፈጻጸም ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ መረጃዎች እንደሚቀርቡ ከአውደ ጥናቱ አስተባባሪዎች ማወቅ ተችሏል።
የተለያዩ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች፣በምግብና ስነ-ምግብ ላይ የሚሰሩ የአለም አቀፍና የሀገር አቀፍ አጋር አካላት፣ የፖሊሲ እና የፕሮግራም አውጪ አካላት በአጠቃላይ ከ150 በላይ የሚሆኑ የጉባኤው ታዳሚዎች በአውደ ጥናቱ የተሳተፉ ሲሆን ከ65 በላይ የምርምር ውጤቶች ቀርበዋል።

. . .በስነ ምግባር የተነጸ አመራር
. . .ከገጽ 1 የዞረ

የተጋረጠባትን ጠላቶቿን የህልውና አደጋ በጽናት ተቋቁማ ወደ ብልጽግና የምታደርገው ጉዞ በሙስናና በብልሹ አሰራር ከቶምውንም ሊደናቀፍ ስለማይገባ ከሌብነት ርቆ በአገልጋይ መሪነት ልብ ህዝብን በጥሩ ስነ -ምግባር ሁሉም አካል ሊያገለግል እንደሚገባ አበክረው ገልጸዋል።
ዶ/ር አማር በርባ አክለውም በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች በዚህ ፈታኝ ወቅት የሀገራችንን ሰላም በማስከበርና ሙስናና ብልሹ አሰራርን በጽናት በመታገል ሀገራችን ወደ ብልጽግና የምታደርገውን ጉዞ በአገልጋይነት መንፈስ ከልብ እንድንደግፍ ይገባል ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።
በዕለቱም የኢንስቲትዩቱ የስነ-ምግባር ና ፀረ ሙስና መከታተያ ዳሬክቶሬት ዳሬክተር አቶ ፉፋ ዳባ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርበው ሰፋ ያለ ውይይት የተካሄደባቸው ሲሆን በቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ዙሪያም በርካታ ሃሳቦች አስተያየቶች ቀርበው ከመድረኩ ምላሽ ተሰጥቷል።



